# አገር እንዴት ሰነበተች  ቁጥር 11     መጋቢት 18 ቀን 2014ዓም(27-03-2022)

አገር እንዴት ሰነበተች  ቅንብራችን  በሳምንቱ  ቀናት ውስጥ በአገራችን ኢትዮጵያ የተከናወኑትንና ሊከናወኑ የታቀዱትን  አበይት ጉዳዮች፣በማንሳት የመረጃ ክፍተት እንዳይኖር ለማድረግ የሚዘጋጅ ሲሆን መረጃዎቹን ተከትሎ ምን መደረግ እንዳለበት የሚያሳስብ ትንታኔና ጥሪ  የሚቀርብበት አምድ ነው።

ለዚህ ስርጭት ጊዜያቸውን ፣ጉልበታቸውን፣እውቀታቸውንና ገንዘባቸውን ሳይሳሱ የሚያውሉት ጥቂት አገር ወዳዶች ለግል ጥቅማቸው ሳይሆን ለጋራ አገር  ህልውናና ለሕዝብ ጥቅም ብሎም የተሻለች ኢትዮጵያን ለቀጣዩ ትውልድ ለማስረከብ ካላቸው የዜጋ ሃላፊነት እንዲሁም ፍጹም ከሆነ አገር ወዳድነትና ሰብአዊነት በመነሳት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።ዝግጅቱን ለማጠናቀር የጊዜ ብቻ ሳይሆን የአዕምሮ ማሰብና ማሰላሰልን ፣ሁኔታዎችን በጽሞና መከታተልንና ማረጋገጥን የሚጠይቅ ሃላፊነት ያለበት ሥራ መሆኑን ሁሉም ይረዳዋል ብለን እናምናለን።ይህ ተግባር ሁሉንም አገር ወዳድ የሚመለከት ስለሆነ ተመሳሳይ አቋምና ፍላጎት ያለው የጥረቱ ተካፋይ በመሆን ለዓላማው መሳካትና ለስርጭቱ መሻሻል  የድርሻውን ለበርከት የሚሻ ቅን አሳቢ በሚከተለው የኢሜል አድራሻ  በመጠቀም እንዲተባበር  የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል በአክብሮት ይጠይቃል።

Ethioandneteditorial 1@gmail.com

ወደ ሳምንታዊው ዘገባ ስናመራ በመጀመሪያ የምንቃኘው  እርእስ በአማራው ብሔር ንቅናቄ(አብን) ውስጥ የተከሰተውን የውስጥ ችግር የሚመለከት ይሆናል።

ችግሩ ለወራት ሲንከባለል የመጣ ሲሆን ጎልቶ የወጣው ግን በምርጫ ቦርድ የተላለፈውን  ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲ በአንድ ወር ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤውን እንዲያካሂድ  የሚለውን ትእዛዝ ተከትሎ በባሕር ዳር ከተማ የአብን ድርጅት ጠቅላላ ስብሰባ ባካሄደበት ወቅት ነው።በመሪዎቹ በኩል እንደተጠበቀው በሰላምና በመግባባት የተጠናቀቀ ሳይሆን አመራሩና ተሰብሳቢው ጎራ ለይቶ የተፋጠጠበት ነበር።ለዚህ ምክንያቱ ከአባላቱ በኩል የፓርቲው መሪዎች የሕዝቡን አደራ በልተዋል፤ ለላካቸው ሕዝብ ሳይሆን ሥልጣን ላጋራቸው የብልጽግና ቡድን አጎብድደዋል፣እጅ ሰጥተዋል የሚል መረር ያለ ክስና ተቃውሞ ተሰንዝሮባቸዋል። ተቃውሞው  ከረር ያለ መሆኑንም የሚያሳዬው መሪዎቹ በሌሎች እንዲተኩ የሚል ጥያቄ ይዞ መነሳቱ ነበር። የሚመለከታቸው የአመራር አባላት ተቃውሞውን ለማብረድ ብዙ ቢጥሩም አልተሳካላቸውም።በመጨረሻም  ጥያቄውን አንቀበልም፤ከሥልጣንም አንወርድም፣ካስፈለገ ከሦስት ወር በኋላ በሌላ ስብሰባ እንወያይበታለን፣አሁን ግን ያለፈውን የስድስት ወር የሥራ ሪፖርት ለማሰማት ስለሆነ በዚያ እንቀጥል የሚል አቋም ያዙ። ብዙሃኑ የቀረበውን ሃሳብ ባለመቀበል  አሻፈረኝ ስላለ አመራሮቹ  የስብሰባ አዳራሹን ጥለው ወጥተዋል።ከወጡም በኋላ ትክክል ያልሆነ መግለጫ አውጥተዋል በማለት ተጨማሪ ተቃውሞ ተነስቶባቸዋል።  ብዙሃኑ ተሰብሳቢ ያቀረበው ተቃውሞና ትችት የአማራው ተወላጅ በዬቦታው  በሚታረድበትና በሚፈናቀልበት ድምጻችሁን ሳታሰሙ ለሥልጣናችሁ  ትኩረት ሰጥታችኋል፤ሕዝቡን ከድታችኋል የሚል ነው። በተጨማሪም የአማራውን ፋኖና ልዩ ሃይል ለማጥፋት መንግሥት በተለይም የአማራው ክልል ብአዴን ሲንቀሳቀስ በዝምታ አልፋችኋል፤ጠይቃችሁ መልስ ካላገኛችሁም ከሥልጣን መውረድ ነበረባችሁ የሚልም ከረር ያለ ትችት ተሰንዝሮባቸዋል።የተሰብሳቢውን ትችትና ተቃውሞ ትክክል የሚያደርገው

የብልጽግና ፓርቲ በአብን አመራሮች ጀርባ መቆሙና የጥበቃ ቡድን መድቦ የስብሰባውን መንፈስ ለመቆጣጠር የሄደበት መንገድ ነው።

ያ ዬት ይደርሳል! የተባለ ጥጃ ድርጅት እንዳለፉት ሁሉ በተመሳሳይ አይነት ውዝግብ ላይ መገኘቱ የአማራው ማህበረሰብ ለተደጋጋሚ ጥቃት እንዲጋለጥ አድርጎታል።እርስ በርሱ እንደ ጃርት እዬተባላ የመሄዱም ነገር በውስጡ ሰው የለም ወይ ያሰኛል።ከዚህ የእርስ በርስ ሽኩቻና ግላዊነት አዙሪት ካልተወጣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም  የአማራው ህልውናና መብት ይረጋገጣል ማለት ዘበት ነው።

ብልጽግና ተብዬው ቡድን በአማራው እልቂትና በመሬቱ ላይ ወያኔና መሰሎቹ ለሚያደርሱት ጥፋት ተባባሪነቱ ጎልቶ በታዬበት፣የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ በተለይም አማራው ነፍጠኛ ተብሎ በእምነቱና በጎሳ ማንነቱ በሚዋከብበት፣ወጣቱ እዬታደነ በእስርቤት በሚወረወርበት በዚህ አስከፊ ጊዜ ከመንግሥት ጋር መሞዳሞድ የወንጀሉ ተጠያቂ ያደርጋል።ስለሆነም የአብንን አመራሮች ቆም ብለው ለሕዝቡ ፍላጎትና ውሳኔ እንዲገዙ ልናሳስባቸው እንወዳለን።አማራን ለመከፋፈልና ለማዳከም ከሚሸረበው ተንኮልና ሴራ እራሳቸውን እንዲያርቁ እንመክራቸዋለን።

የዚህ አይነቱ ችግር በተደጋጋሚ ታይቷል።ወደፊትም አይታይም ተብሎ አይጠበቅም።ምክንያቱም ግለሰብም ሆነ ቡድን በሚለውና በሚጽፈው ፕሮግራም ብቻ ተማምኖ ሃላፊነትና አመራር ቦታ ሰጥቶ ፣ እያጨበጨቡ ምራን ማለቱ  የሚያመጣው ጣጣ ነው።የትኛውም ድርጅት ሆነ ማንኛውም  የአመራር አባል የሚሆን ከሹመቱ  በፊት በተግባር መፈተን አለበት። ሄዶ ሄዶም ከተገለበጠ ድጋፍ መንሳትና ከሹመቱ ማንሳት ተገቢ ነው።መራጩ ሕዝብ በቃኸኝ ውረድ ካለም ጓዜን ጨርቄን ሳይሉ መውረድ ግዴታ ነው።

ምንም እንኳን አብዛኛውን ጊዜ ችግር የሚፈጠረው ከድርጅትና ከአመራር በኩል ቢሆንም በመራጩ ሕዝብ በኩልም ባሉና በሚፈጠሩ ድክመቶችና ስህተቶች ምክንያት ድርጅት ሊፈርስና መሪዎችም ለአደጋ ሊጋለጡ እንደሚችሉ ማመን ያስፈልጋል።ባልተረጋገጠ ቅስቀሳ ወይም በሰፈር ልጅነት ወይም በጎጥ እይታ  የአገርና የሕዝብን አደራና ጥቅም መለወጥ ብዙ ዋጋ ያስከፈለ ሲሆን ወደፊት ካልታረመ ለተመሳሳይ ችግር ይዳርጋል።ጠላቶች የሚገቡበት ደካማ በር ቢኖር ጎጠኝነትን ተከትሎ በሚፈጠር ውዝግብ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የአማራው ማህበረሰብ ከደረሰበት ተደጋጋሚ አሮንቋ መውጣት አለበት። ያም የሚተገበረው በቆራጥና በትግል በተፈተኑ አገር ወዳዶች ሲመራ ብቻ ነው።ኢትዮጵያ ከሥልጣን፣ ከጎጥና ከጎሳ እንዲሁም ከሃይማኖት በላይ ነች!በዛ ገመድ ውስጥ መተብተብ ለባሰ ችግርና መከራ፣ ለእርስ በርስ ግጭት ብሎም ለጠላቶች ፍላጎት መሳካት ያጋልጣል።

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያዊነት እዬደበዘዘ ጎሰኝነት እየጎላ መምጣቱን የሚያመላክተው  በየክልሉ ጎሳ ስም የተደራጁት ምክር ቤቶች በስብሰባ መጠመዳቸው ነው።የአማራው ብሔራዊ ምክርቤት፣የጨፌ ኦሮሚያ ምክር ቤት፣የደቡብ ሕዝቦች ምክር ቤት፣የአፋር ሕዝብ ምክር ቤት፣የሶማሊያ ክልል ምክርቤት---ወዘተ የተባሉት  አገር አቀፍ ነው ከተባለው የብልጽግና ፓርቲ  የሚለይበት መልኩ በስም እንጂ በአወቃቀር እንዳልሆነ  በሁለቱም በኩል ያለው አሰላለፍና ጥምረት ያረጋግጣል።ለዚያም ነው ክልሎችም ብልጽግናም የሚተዳደሩበትን ሕገመንግሥትና አገራዊ አወቃቀር የሙጥኝ ያሉት።የያዙት የጎሳ ፖለቲካና አገራዊ የክልል አወቃቀር እስከነ ሕገመንግሥታዊ መመሪያውና አስተሳሰቡ ካልተወገደ በስተቀር ኢትዮጵያ እንደ አንድ ልዑላዊ አገር የመቀጠሏ ዕድሏ የመነመነ ነው።ለዚያም ነው ሥር ነቀል ለውጥ መምጣት አለበት የሚባለው።በአብዮታዊ ዴሞክራሲም ሆነ በመደመር ትርክት የተሻለች ኢትዮጵያን ማረጋገጥ አይቻልም።

ሌሌኛው የሰሞኑ እይታችን የሚያተኩረው

በሰሜኑ ያገራችን ክፍል የወያኔ ጥቃት እዬጨመረ መሄዱን የሚያመላክተው ነው።በሁመራ በኩል ሱዳን ውስጥ ያዘጋጃቸው ሃይሎች ሰርገው ለመግባት ተደጋጋሚ ሙከራ ያደረጉ ሲሆን በከባድ መሣሪያ የታገዘው ወያኔ ከሱዳን ድንበር ተነስቶ ጥቃት ለመፈጸም መቻሉ በጦርነቱ የሱዳኖች ተሳትፎ መኖሩን ያረጋግጣል። የትኛውም አገር በድንበሩ ዙሪያ የሠፈረ ሃይል የሌላውን አገር እንዲያጠቃ ከፈቀደ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የጦርነቱ ተካፋይ ተደርጎ ይቆጠራል። ወያኔ፣በወልቃይት፣በራያና አዘቦ እንዲሁም በአፋር በኩል የያዘውን መሬት እያሰፋ በመሄድ ላይ ሲሆን ብዙ ዜናችም ተፈናቅለዋል። በተለይም የአፋር ወገኖቻችን ከደረሰባቸው ድቀት ሳያገግሙ ለተደጋጋሚ ጥቃት ተጋልጠው የመንግሥት ያለህ እያሉ ጥሪ ቢያሰሙም መንግሥት ተብዬው በተለመደው ዝምታው ቸል ብሏቸዋል። የብልጽግና ቡድን የተጠመደው አስረሽ ምችው ድግሥና ፌስታ በማዘጋጀቱ ላይ ነው።

የኦሮሙማው ክልል  የኦሕዴድ ብልጽግና መሪ ነኝ ባዩ ሽመልስ አብዲሳ እንደ ሌሎቹ ክልሎች በጠራው ጠቅላላ ጉባኤ ጨፌ ኦሮሚያ በሚል መጠሪያ  በመስከ መካከል በተዘጋጀ ድግስ የተከፈተውን ጉባኤውን አጠናቋል። ሽመልስ አብዲሳ በጉባኤው ላይ ለተሰብሳቢው ባደረገው ንግግር የኦሮሙማ ጉዞ በስኬት ላይ እንዳለ፣አብይ አህመድን የመሰለ መሪ ከኦሮሞ ማህጸን ማግኘት የሚያኮራ መሆኑን በመግለጽ ስሜት ቀስቃሽ ንግግር አድርጓል።በመቀጠልም ኦሕዴድ ብልጽግና “ጋጮና ሲርና” የሚል አዋጅ ማውጣቱን ይፋ አድርጓል።ይህ አዋጅ ሁሉም የኦሮሞ ተወላጅ መሣሪያ እንዲታጠቅ የሚፈቅድ ሕግ ሲሆን መሠረቱም የአባ ገዳ ሥርዓት ነው ብሏል።ሌላው ክልል በተለይም አማራው ትጥቅ እንዲፈታ በመንግሥት ተብዬው ሲገደድ ፣የመንግሥትን ሥልጣን የበላይነቱን በተቆጣጠረው አነጋዊ ኦሮሙማ ፓርቲ በኩል የወጣው አዋጅ ማንን ለመምታት ታስቦ እንደሆነ በግልጽ ይታወቃል። የክልሉ መሪ ሽመልስ አብዲሳ በዚህ ብቻም አልቆመም።አዲስ አበባን ኦሮሞ የማድረጉ ሥራ በመጠናቀቅ ላይ ነው ሲልም ደጋፊዎቹን እንኳን ደስ አላችሁ፣ ሌላውን ተቃዋሚ ኢትዮጵያዊ በተለይም አዲስ አበቤን ደግሞ እርማችሁን አውጡ ብሏል።ይህ የእብሪተኞች ተረኛ ቡድን መረን የለቀቀ አካሄድ በሁሉም አቅጣጫ ታይቷል።ባለፈው ስርጭታችን የቀረበው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በአማራው ተወላጅ  ተማሪዎች ላይ የደረሰው ጥቃት፣በዬትምህርት ቤቱ ግቢ የኦሮሞ አባገዳ ባንዲራ እንዲሰቀል ማድረግ የዚሁ አዲስ አበባን የመሰልቀጡ ሂደት አካል ነው።ይህንን  መረዳትና የከፋ አደጋ ሳይመጣ መከላከሉ አስፈላጊ ነው እንላለን።

ይኸው ሃፍረተቢስ በመንግሥት ቸልታና በመከላከያ ሹማምንቱ ተባባሪነት ወያኔ በወረራ የአማራውንና የአፋሩን መኖሪያ እያወደመ ሰሜን ሸዋ ጣምራ በር ሲደርስ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሶ ሕይወቱን ገብሮ ያገኘውንም ድል በቁሮ መስዋእትነት የተገኘ ነው ሲል የሌሎቹን ተሳትፎ እንዳልነበረ አድርጎታል።  እንዲህ ነው የኦሮሙማው ቡድን ክህደትና የኬኛ ፖለቲካ።

ከኦሮሙማው የተረኝነት መንፈስ የሚቀዳው ጸረ አማራ ሴራ በአብይ አህመድ የደህንነት መዋቅር የተከፈተው የአማራ ፋኖንና የልዩ ሃይሉን የማዳከምና የማጥፋት  ዘመቻ ተጠናክሮ ቀጥሏል።የልዩ ሃይል አዛዥ የሆነውን ጀነራሌ ተፈራ ማሞን ማባረሩን ተከትሎ ለማሰር ዝግጅቱን የጨረሰ ሲሆን ለእርምጃው እንቅፋት ይሆናሉ ያላቸውንም የተከዜ ብርጌድ በመባል ግዳጅ ላይ ያሉትን ለማፈን ወይም ለመበተን የደመወዝ ክፍያ ማቆሙ የሰማነው አንዱ አሳዛኝ ዜና ነው። የልዩ ሃይሉ አባላት ችግራቸውን በሰላማዊ መንገድ ለክልሉ አስተዳደር ለማሰማት በጉዞ ላይ እንዳሉ የታገዱ ሲሆን ከመካከላቸውም ለእስር የተዳረጉ መኖራቸው ተሰምቷል።ይህንን በደል የፈጸመው በአማራው ስም የኦሕዴድ ተላላኪ የሆነው ብአዴን ነው።የአብይ አህመድ አሕዴድ መራሹ ብልጽግና ለሚፈልገው ዓላማ ከቻለ ደካማውን

በጥቅማ ጥቅም መያዝና የሚፈልገውን ማድረግ፣ አለያም አልበገር ያለውን በጉልበት ለማንበርከክ እንደሚንቀሳቀስ በተደጋጋሚ የታዘብነው ሃቅ ነው። ይህ በእንዲህ እያለ፣

የኦሮሙማው ብልጽግና የኦነጉ የሸብር ክንፍ በወለጋና በተለያዩ ቦታዎች በአማራው ተወላጅ ላይ የሚያደርሰው ጥቃት ከቀን ወደ ቀን እይጨመረ በመሄድ ላይ ነው።ሞትና መፈናቀል የዘወትር ዜና ከሆነ ቆይቷል።በመተሃራ ወጣቶች በሰላም ተሰባስበው በሚጫወቱበት ቦታ የኦነግ አሸባሪ ቡድን ከአስራ አምስት በላይ ወጣቶችን በግፍ ጨፍጭፏል።ከነዚህም ውስጥ 13 የአማራ፣ሁለት የደቡብ ማህበረሰብ ተወላጆች ናቸው።ይኸው አሸባሪ ቡድን በአምቦ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚገኝ መንደር ገብቶ ንጹሃንን ረሽኗል።ከረሸናቸው ውስጥ አቶ ተፈሪ ሃይሉ የተባሉ የመቶ ዓመት አዛውንት ይገኙበታል።የዚህ አይነት ጭካኔ መፈጸም እንደ ጀግንነት የሚቆጥር አረመኔ ቡድን ወይም ደጋፊ በሰው ተራ ለመታዬት መስፈርቱ አይፈቅድለትም።ከአውሬ የባሰ አውሬ ነው።አውሬ እንኳን ከሰው ጋር ለምዶ ለመኖር ችሎታና ብቃት አለው።እነዚህ ኦነጋውያን ግን ቁመናቸው በሰው ምስል መንፈሳቸው ከሰይጣን ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም። ሆድ ተቀዶ ጽንስ ሲወረወር፣መነኩሴና ህጻን ልጅ ሲደፈር፣ሰው እንደ ከብት ሲታረድ፣የሰው ኩላሊት ሲበላ የታዬው፣በሃይማኖት በታወቀች፣ክርስቲያንና ሙስሊም በሚኖሩባት በእኛው አገር በኢትዮጵያ ምድር በበቀሉ አረመኔዎች ነው። ይህ አይነቱ ጭካኔ በመጀመሪያው የሰው ልጅ የፍጥረት ደረጃ ላይ፣በዛፍ ላይና በሸለቆ ውስጥ በሚኖርበት ዘመነ ፍጥረት እንኳን ያልታዬ ነው። ከዬትና፣እንዴት ለምንስ እንደመጣ መጠናት አለበት።ምንጩ ካልታወቀና ካልተወገደ ለአገራችንና ለሕዝቧ መጥፎ ገጽና አሳፋሪ ታሪክ ከማላበሱም ባለፈ ለሌላው ዓለም ሕዝብ መጥፎ ልማድና ባሕል ያወርሳል። ኦሮሙማይዝም ከፋሽዝም ወይም ከአውሬነት(አውሬይዝም) የበለጠ መሆኑን አምኖ መቀበል ብቻ ሳይሆን እንዳይስፋፋና ተቀባይነት እንዳይኖረው በብርቱ መቃወምና መታገል ያስፈልጋል። የኦሮሙማይዝምን እኩይ ድርጊት የሚኮንን የኦሮሞ ተወላጅም ሆነ የሌላው ማህበረሰብ ተወላጅ ለራሱ ታሪክ ሲል በስሙ የሚፈጸመውን ጭፍጨፋና ኢሰብአዊ ድርጊት ሊቃወም ይገባል፤በተጠያቂዎቹም ላይ እርምጃ በመውሰድ ማህበረሰቡን ማጽዳት ይጠበቅበታል። ያ ካልሆነ ግን ከ16ኛው ዘመን ከተፈጸመው የወንጀል ተግባር በ21ኛው ክፍለዘመን የተፈጸመው አረመኔያዊነት የኦሮሞን ማህበረሰብ ሲያሳፍር የሚኖር ታሪክ ይሆናል።ሌላውም ተመሳሳይ ድርጊት የሚፈጽም ማህበረሰብ የተለዬ ታሪክ አይኖረውም።

ሌላው የሰሞኑ አነጋጋሪ ጉዳይ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናን ውጤት ተከትሎ የተነሳው ውዝግብ ነው።ውዝግቡ የተነሳው በአማራ ማህበረሰብ ለፈተና ለቀረቡት ተማሪዎች፣ አምጥታችኋል ተብሎ የተሰጣቸው ውጤት ሲሆን ለማለፍ ብቻ ሳይሆን ለከፍተኛ ደረጃ የታሰቡ ልጆች ላይ መሆኑ የውጤቱ ማሽቆልቆል ተንኮል አዘል አድርጎታል።በተለይም በአማራው ክልል ተማሪዎች ላይ መሆኑ ትውልድን ከእውቀት ማማ የሚያወርድ፣ተስፋን ለማጨናገፍ የተደረገ እኩይ ተግባር ሆኖ ተገኝቷል። የተሰጣቸው ውጤቱ እንደገና እንዲታይላቸው ብዙ ቢጠይቁም ተገቢ መልስ ሳያገኙ የቀሩ ብዙ ናቸው።የጥቂቶቹ ግን ሲመረመር የአገሪቱን የፈተና ውጤት በከፍተኛ ነጥብ የሰቀሉ መሆናቸው ተረጋግጧል።በአማራው ላይ የተመዘዘው የማጥቃት ዘመቻ በሁሉም አቅጣጫ መሆኑን ይህ ሌላው ማስረጃ ነው።መብራት እንደ ልብ በማይገኝበት፣ሰላም ባልሰፈነበት አካባቢ እዬኖሩ ለዚህ ከፍተኛ ውጤት መብቃት የአማራውን ልጆች ብቃትና የተፈጥሮ ችሎታ የሚያሳይ ነው።ሁሉም ኢትዮጵያዊ በተለይም አማራው በነዚህ ወጣቶች ሊኮራ ይገባዋል።ወጣቶቹም ለቁም ነገር እንዲበቁ፣ትምህርታቸው ለእንጀራ ብቻ ሳይሆን ሕዝብን ለማገልገል፣እንዲህ አይነቱን ትውልድና አገር ገዳይ ድርጊት ለማሶገድ እንዲጠቀሙበት እንመኛለን። ከዚህ ጋር ተያይዞ የተሰማው አሳፋሪ ወሬ የኦሮሚያ ክልል ባለሥልጣናት በትምህርት ተቋሙ ላይ ጫና ማድረጋቸው ነው።በዚህም ጫና ምክንያት ነጥባቸው

ከወለል በታች የሆኑት እንዲያልፉ መደረጉ ነው።አሮሞን ጠቀምን ሲሉ ገደል እዩከተቱት መሆናቸውን ሌላው የጎሳው ተወላጅ ሊያውቀው ይገባል።

ለአገር ደንታ የሌለው ቡድን በሥልጣን ላይ ከተቀመጠ ሁሉም ነገር መላ ቅጡ ይጠፋል፤ትምህርት ኤኮኖሚው፣ ፖለቲካው፣የማህበረሰብ እሴቱ፣ባህልና ወጉ ገደል ይገባል።የማታ ማታም አገር የሚባለው ትልቅ የጋራ ሃብት በሽርፍራፊ መንደር ይቀዬራል።የአገራችን አቅጣጫ ይህንኑ ስለሚያመለክት ሳይመሽ መስመር ማስያዙ ለሁሉም ይጠቅማል።የሌሎችም አገሮች የመፈራረስ ሂደት የተጠናቀቀው አሁን በአገራችን የሚካሄደውን አይነት ተከትሎ መሆኑን ብዙሃኑ የሚመሰክሩት ሃቅ ነው።የእኛም እይታ ከዚያ አይርቅም።

ኢትዮጵያን ለማፍረስ የውስጥና የውጭ ሃይሎች ተባብረዋል።በሚፈልጉት ቀለበት ውስጥ የማስገባቱ ሙከራ ካልተሳካላቸው ብትንትኗ ቢወጣ ደንታ የላቸውም። ምዕራባውያን እንኳንስ ለአፍሪካ ለአውሮፓውያኑም አልተመለሱም።የዩጎዝላቪያ መበታተን ለዚያ ምስክር ነው።ኮሪያን ለሁለት መሰንጠቅ፣ኮንጎንም እንዲሁ አጋድሎ የሁለት አገር ዜጋ ማድረግ የዚያው የወራሪዎች ፍላጎት ውጤት ነው።ወያኔ፣አነግና ተባባሪዎቹ ከውስጥ፣ በአሜሪካና በአውሮፓ የሚደገፈው የግብጽ መራሹ የሱዳን ወራሪ ከውጭ ሆነው በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸውን ከተገነዘብን ውሎ አድሯል።በዲፕሎማሲና በጥቅማ ጥቅም ለመደለልም ብዙ መሞከሩን ታዝበናል፣እዬሞከሩም ነው።ሰሞኑን የአሜሪካው ተላላኪ ዴቪድ ሳተርፊልድ(David Saterfield) ከናይጀሪያው አቻው ከአባሳንጆ ጋር ከተወያዬ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ ተሰምቷል። የተለዬ መፍትሔ ይዞ የሚመጣ ነው ተብሎ አይጠበቅም።ምንም እንኳን የንግግሩ ይዘትና ውጤት ባይታወቅም ያንኑ የአሜሪካኖቹን የእቀባ ዱላውን ለማሳዬት መሆኑ ግልጽ ነው።ጎን ለጎንም የአሜሪካ የኮንግሬስ አባላት በኢትዮጵያ ላይ ጠንካራ እቀባ ለማድረግ HR6600 የተሰኘ ረቂቅ አዘጋጅተው ለማጽደቅ ተዘጋጅተዋል።ውሳኔው በፕሬዚደንቱ በባይደን ፊርማ እንደሚጸድቅ ይጠበቃል።ይህ HR 6600 በመባል የረቀቀው የእቀባ አንቀጽ በሰብአዊ መብት ጥሰት ላይ ተሳትፈዋል የሚላቸውን ግለሰቦችና ባለሥልጣኖች ተጠያቂ የሚያደርግና ኢትዮጵያም ተባባሪ ካልሆነች ከማንኛውም የዓለም አቀፍ ድርጅት እርዳታና ብድር እንዳታገኝ የሚያግድ ነው። ያም ብቻ ሳይሆን በሰብአዊ መብት ጥሰት በተጠረጠሩ ሰዎች ላይ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል እንደሆነ የአንቀጹ እረቂቅ ያስረዳል።የኢትዮጵያ መንግሥትም በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተለይም በአሜሪካ ያሉት ሕጉ እንዳያልፍ ተቃውሞ እንዲያሰሙ ጥሪ አድርጓል።በሳንፍራንሲስኮ የሚኖሩትም የሥርዓቱ ደጋፊዎች የሆኑ ኢትዮጵያውያንና የኤርትራ ተወላጆች ሰልፍ አድርገዋል።ውጤት ያመጣል ተብሎ ግን አይጠበቅም።አሜሪካኖቹ የሚፈልጉትን ካላገኙ በስተቀር ወደ ኋላ አይሉም።

እርግጥ ነው የረቀቀው አንቀጽ በምክር ቤቱና በሴኔቱ አባላት ድጋፍ ካለፈና ፕሬዚደንቱ በፊርማው ካጸደቀ ተግባራዊ ይሆናል።ጥያቄው ግን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባያልፍ የሚሰጠው ጥቅምና ቢያልፍ ደግሞ የሚደርስበት ጉዳት ምን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ ለመደገፍም ሆነ ለመቃወም ያመቻል። ያንንም ለማወቅ የሕጉን ረቂቅ በሚከተሉት ጥያቄዎች መፈተሽ ይኖርበታል።

እስከ አሁን ድረስ ከውጭ አገር የሚገኘው እርዳታና ብድር ለሕዝቡ የሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?እስከዛሬስ በተገኙት ግብአቶች ማን ተጠቀመ?ሕዝቡ ከርሃብና ከድህነት ወጥቷል ወይ? ወይስ መሪዎች ለሚመሩት ቅንጡ ኑሮና በውጭ አገር ለሚገዙት ንብረት ዋለ? የእስከዛሬው እርዳታና ብድር ዬት ገባ? ምንስ ተሠራበት?የሚለውን ማንሳት ለሚያዘው አቋም መመዘኛ ነው።በእኛ በኩል የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠቃሚ አይደለም ስለሆነም ብድርና እርዳታ ቢመጣ ቢቀር የሚለውጠው ነገር አይኖርም የሚል አቋም አለን።ስለ ወንጀለኞቹ ተጠያቂነት የምንሻው ስለሆነ እውነት ካደረጉት አበጃችሁ የምንላቸው ይሆናል።የአሜሪካኖቹ አካሄድ ግን ወያኔንና ተባባሪዎቹን በሚጠቅም መልኩ ለመተግበር

የታለመ ለመሆኑ ከአነሳሳቸው ለመረዳት ችለናል።ለእነሱ በደቡብና በኦሮሚያ፣በቤንሻንጉልና በሌላው ክልል ውስጥ የሚጨፈጨፈው ኢትዮጵያዊ በተለይም አማራው ከግምታቸው ውስጥ አይገባም።ለነሱ ጭፍጨፋና የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚሉት በሚደግፉት  ህወሃትላይ፣ በትግራይ ውስጥ የተፈጸመውን ብቻ እንጂ በሌላው ከባቢ  በተለይም በአማራው ማህበረሰብ ላይ የሚፈጸመውን አይደለም።እርግጥ ነው በትግራይ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ላይ  የተፈጸመው ጭፍጨፋም ወንጀል ነው፤የፈጸሙትና ያስፈጸሙት ለፍርድ መቅረብ አለባቸው።ግን ወያኔና ተባባሪዎቹ በሌላው ያገሪቱ ክፍል ለፈጸሙት የዘር ማጥፋት ወንጀል ማካካሻና ሽፋን መሆን አይኖርበትም።የአንዱ ሕይወት ከሌላው ህይወት አይበልጥም፤ የአንዱ ደም ከሌላው ደምም አይቀጥንም።

ብንታደል ኖረማ በመጀመሪያ ላይ እንዲህ አይነት ዘር ተኮር ጭፍጨፋ ባልተፈጸመ ነበር፤ከተፈጸመም በራሳችን ሕግና ፍርድ ቤት ወንጀለኞቹ  ቅጣታቸውን ባገኙ ነበር።የዓለም ፍርድ ቤት ተብዬው ጥርሱን የሚያሳዬው የምዕራባውያን ጥቅምና ፍላጎት ሲነካ ብቻ ነው።እነሱ በሚፈጽሙትና በሚያስፈጽሙት ወንጀል ላይ ክስ አይመሰርትም።ሆነም ቀረም በሰብአዊ መብት ጥሰት የሚጠዬቁት የትም ይሁን መቼም ተጠፍረው ለፍርድ ቢቀርቡ የምንሻው  በመሆኑ ለምን ብለን አንቃወምም።

የአሜሪካኖቹ የበቀል እርምጃ ያሰጋው የአሕዴድ መራሹ መንግሥት ያለምንም ቅድመሁኔታ ከወያኔ ጋር ለመደራደርና የእርዳታ አቅርቦትም ካለምንም እገዳና ፍተሻ ወደ ትግራይ እንዲገባ መወሰኑን ይፋ አድርጓል።ያላካሄደውን ጦርነት አቁሜያለሁ ማለቱ እራሱ በሰራው ፊልም የሚረካ ተመልካች ከማድረጉ በቀር የሚያታልለው አካል አይኖርም።ጦርነቱ ተጠናቋል ብሎ ካወጀ ወራቶች አልፈዋል። ጦርነቱን ያልጨረሰው ወያኔ ብቻ ነው።መግለጫው ከሕዝብ ጆሮ ሳይደርስ የአሜሪካና የእንግሊዝ፣ የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሃፊ ጉተሬዝ፣የአፍሪካ ህብረትና የአውሮፓ ህብረት  እዬተቀባበሉ መንግሥትን አወድሰዋል። የሚፈልጉትን በማግኘታቸው ሊደሰቱ ይገባል።ኢት൦Peያን በመዳፋቸው የማድረግ ዓላማቸው ተሳክቶላቸዋል።ነገ ደግሞ የትግራይና የሌሎቹ ተገንጣይ ሃይሎች ጥያቄ እንዲመለስ ብለው መጠዬቃቸው አይቀርም።የአባይም ግድብ እንіhu ከግብጽ ጥቅም ጋር ተሳስሮ እንዲፈታ የማድረግ እንቅስቃሴያቸው እንደማይቀጥል ዋስትና የለም።

የብልጽግና መሪዎች ከእስራት ነጻ መሆናቸውና ና እንደልብ አውሮፓና አሜሪካ ለመንሸራሸራቸው የሚያስችል መብት ካገኙ ኢትዮጵያ ብትኖር ባትኖር  ደንታቸው አይደለም።የሚቀርበውን የባዕዳኑን ጥያቄ ሙሉ ለሙሉ ከመመለስ ወደ ኋላ አይሉም።

ለአገራችን ዘላቂ ሰላም፣አንድነትና እድገት ከምዕራቡ ማነቆ መውጣት እንጂ በብድርና በእርዳታ ስም በመዳፋቸው ውስጥ መግባቱ ለሚፈልጉት ጥቃትና እርምጃ  እንደሚያጋልጠን ይህ መንደርደሪያ ነው።

በወያኔዎቹ በኩል ግን የተጠዬቁትን ለማሟላት ያሳዩት ፈቃደኝነት የለም።አሁንም የራያና አዘቦ፣ የወልቃይትና ጠገዴ ለም መሬት ይገባናል ባዮች ናቸው።ወረራውንም የሚያካሂዱት ለዚያ ስምምነት ከጠንካራ ቁመና ላይ ለመገኘት ነው።የአብይ አህመድ መንግሥት ይህንንም ጥያቄያቸውን ሙሉ ለሙሉ እንደሚቀበለው እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል።ለአብይ አህመድ የሥልጣን ወንበሩ እንጂ ሌላው ያገሪቱ ልዑላዊነት የሚያስጨንቀው አይደለም።ከወያኔ ጋር ለሰላሳ ዓመታት  ያስተሳሰራቸው የጸረ ኢትዮጵያ የሆነው አቋማቸው  ስለሆነ ተጣልተው አይጣሉም። ወይም እንደ ዱሮው ተስማምተው በጋራ ሲጨቁኑና ሲበዘብዙ ይኖራሉ፣አለያም አገር አፍርሰው የሌላውን ከባቢ ቦጫጭቀው ክልላቸውን አስፍተው፣አገር ሆነው ይኖራሉ።ይህ ሊሆን የሚችለው ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለው ሃይል ካልጠነከረና በአንድ መቆም ካቃተው ነው።ለብሔራዊው ክብራችንና ለጋራ ጥቅማችን ሌላው ብቸኛ አማራጭና  ዋስትና እራሳችንን  የምንችልበትን ጥገኛ ያልሆነ ሥርዓትና ብሔራዊ ኤኮኖሚ መገንባት

ነው እንላለን። ለዚያ መንደርደሪያችን አሁን የሰፈነውን የጎሳ ፖለቲካና ሥርዓት አሽቀንጥሮ መጣል ነው።በምትኩ የሕዝብ በሕዝብ ለሕዝብ የሆነ መንግሥት መመሥረት ነው።

ወደ ቀጣዩ እርእስ ስናልፍ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ከከተማዋ አስተዳደር ጋር ያደረጉትን ስብሰባ የሚመለከት ይሆናል።በዚህ ስብሰባ ላይ ብዙና ጠንከር ያሉ ሕዝባዊ ጥያቄዎች ተነስተዋል። በአስተዳደሩ ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች መካከል የታዩም አቀራረቦች ታዝበናል።በአጠቃላይ ሲታይ ስብሰባው ካለፉት ሁሉ የተለዩ ነበር ማለት ይቻላል። ምንም እንኳን አጥጋቢ መልስ ባይሰጥባቸውም የሕዝቡ ብሶቶች ግልጥልጥ ብለው ቀርበዋል። ነገ ሕዝቡ ምን እርምጃ ሊወስድ እንደሚችል አመላካች ነው። በመጨረሻውም በንትርክ የተዋጠው ስብሰባ በውሳኔ ሳይቋጭ መበተኑ ታውቋል።

ከሕዝቡ ጥያቄና ተቃውሞ ሳንወጣ በጎጃም ከ/ሃገርም አርሶ አደሮች በማዳበሪያ ዋጋ ውድነት የተነሳ ጥያቄ ይዘው አደባባይ የወጡበት ሳምንት ነው።በምሥራቅ ጎጃም ተጀምሮ ወደ ምዕራቡ የተሸጋገረው የአርሶ አደሮች ጥያቄ ለኩርማን መሬት ማዳበሪያ ከአራት ሽህ ብር በላይ መጠየቃቸውና ሁለት ዓመት ያመረቱትን በሙሉ ቢሸጡ እንኳን የተጠዬቁትን መክፈል እንደማይችሉ በምሬት ገልጸዋል።ኢትዮጵያን የሚያክል የሰፊ ለም መሬት ባለቤት የሆነው አርሶ አደር ለባዕዳን ማዳበሪያ መጋለጡ ከውርደት ውርደት ይቆጠራል።ኢትዮጵያ የራሷን ማዳበሪያ ለመምረት የምትችል ብትሆንም ከዚህ የንግድ ሰንሰለት የሚጠቀሙ የእርሻ ባለሥልጣኖች፣ባለሙያዎችና ነጋዴዎች ውሳኔ አገራችንና አርሶ አደሩ የውጭ አገር ማዳበሪያ ጥገኛ እንዲሆንና ለችግር መጋለጡ የአገራዊ ቀውሱን ልክና መጠን ያሳያል። ለዘመናት የሰለጠነው የእርሻ ባለሙያና ሊቃውንት ምን እንደዋጠው ሲያስቡት ይዘገንናል።የእርዳታ እጅ ጠብቆ ማደሩን ሲያስቡት ደግሞ አገር ወዳዱን የበለጠ ህመም ላይ ይጥላል።

ከጎጃም ሳንወጣ በፈተናው ውጤት ምክንያት የተማሪዎችና የመምህራን ተቃውሞ የተቀሰቀሰበት ሳምንት ነው።መምህራንና ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የከተማው ነዋሪ የተቀላቀለበት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለመሆን ችሏል።ለቀጣይ ሕዝባዊ ተቃውሞ ዝግጅቱ የቀጠለ ሲሆን በመላው የአማራ ክልል አዲስ አበባን ጨምሮ ለማቀጣጠል ጥሪ ተላልፏል። የአማራ ክልል መንግሥታዊ ተቋም ሰልፉ እንዳይካሄድ ከተካሄደም ለሚደርሰው ችግር ተጠያቂ እንደማይሆን መግለጫ አውጥቷል።ይህ የሚያሳዬው መንግሥት ነኝ ባዩ የብአዴን ኦሕዴድ ተላላኪ ቡድን እርምጃ ለመውሰድ ማቀዱን ነው።

ካፈርኩ አይመልሰኝ ያለው መንግሥት ተብዬው የኦሕዴድ አስተዳደር በአዲስ አበባ ከተማ የጀመረውን ወጣቱን የማሳደድ እርምጃ በሰፊው ቀጥሏል።ብዙዎቹ የገቡበት ባለመታወቁ ቤተሰብን ጭንቀትና ስጋት ላይ ጥሏል።የኑሮ ውድነቱ፣ሰላም ማጣቱ፣ፍትሕ አልባነቱ ፣ሥራ አጥነቱ፣ተስፋ ቢስነቱ በአጠቃላይ የሰፈነው ችግር ሲታይ የሕዝቡ ብሶት ዋንጫው ሞልቶ፣ሕዝባዊ ተቃውሞና እምቢ ባይነት ገንፍሎ ለመውጣት ከቋፍ ላይ የደረሰ ይመስላል።ይህ የሕዝብ እምቢ ባይነት በድል አድራጊነት እንዲጠናቀቅ በተደራጀ መልኩ የሚመራ ሕዝባዊ ኮሚቴ ይቋቋም የሚለው የዘወትሩ ጥሪያችን የአሁኑም ጥሪያችን ነው።የሁሉንም ብሶትና ምሬት ስንደማምረው አገራችን የምትጓዝበት የጎሰኞች ባቡር ተንገጫግጮ ከሚንኮታኮትበት ገደል ጠርዝ ላይ እዬቀረበ መምጣቱን የሚያሳዩ ቢጫ መብራቶች እዬበሩ መሆኑን ታዝበናል።ይህ የጎሰኞች ባቡር ገደል ሲገባ ተሳፋሪው ሕዝብ አብሮ ገደል እንዳይገባ ቀድሞ መውረድ እራስንና አገርን ማዳን መሆኑን ለማሳሰብ እንወዳለን። በኢትዮጵያዊነት ባቡር ላይ ተሳፈሩ የሚለው የወቅቱ ጥሪያችን ነው።

ከአዲስ አበባው አስተዳደር ስብሰባ ቀጥሎ የአማራው ክልል አስተዳደር በባሕርዳር ከተማ ዓመታዊ ጉባኤውን አካሂዷል።በዚህ ጉባኤ ላይ ብዙ ብሶቶች የተስተናገዱበት ሲሆን በአጽንኦት ግን በአማራው ማህበረሰብ ላይ የሚደርሰው መጠነ ሰፊ ጥቃት ላይ መንግሥት ተብዬው አካል ምንም አይነት

መፍትሔ እንዳልሰጠው ይባስ ብሎም ችግሩን በማቃለል ላይ እንደተሰማራ የሚያጋልጥ ነበር።በጥቂት ደፋሮች በኩል በአማራው ማህበረሰብ ላይ ከመሬት ወረራና ማፈናቀል፣ ከኤኮኖሚ ተጠቃሚነት፣እስከ ማንነት ህልውና፣ከማንነት ህልውና እስከ ዘር ማጥፋትና ማቀጨጭ በደል የተፈጸመው በመንግሥታዊ ሴራ መሆኑ ዝርግፍ ብሎ የወጣበት ስብሰባ ነበር። የክልሉ ርዕሰ ብሔር ለቀረቡት ጥያቄዎችና በደሎች ተገቢው መልስ ይሰጣል በሚል ማምለጫ ቃል የቋጨው ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ የተሰብሳቢውንና የአማራውን ማህበረሰብ ያረካል ተብሎ አይጠበቅም።

ሰሞኑን በያቅጣጫው የታዬው የሕዝብ ብሶት በቀጣዩ ምን ይዞ እንደሚመጣ የምናዬው ቢሆንም በእርግጠኛነት ግን ነገሮች እንደነበሩ እንደማይቀጥሉ ነው።

ሌላው ኦሕዴድ መራሹ ቡድን ከወያኔ ጋር ለመደራደር የወሰደውን እርምጃ ተከትሎ ከኤርትራው መሪ ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር የተፈጠረው መፋጠጥ ነው።አብይ አህመድ እንኳንስ ሌላውን ልጆቹንም ቢሆን ለሚፈልገው ጥቅሙ አሳልፎ ይሰጣል፣ይክዳል።ኢሳያስንም ማኖ ካስነካ በኋላ ለዓለም አቀፉ የቅጣት ምት ብቻውን አጋልጦታል።እራሱን ከወንጀል ክስ ሲያወጣ (ለጊዜውም ቢሆን)ኢሳያስን በብቸኛ ተጠያቂነት ሜዳ ላይ ዘርሮታል።ይህ የማይዋጥለት ኢሳያስ ምላሹ ምን ሊሆን እንደሚችል ባይታወቅም እሱም ከሱዳንና ግብጾች ጋር ሊጫወትበት የሚችለውን ካርታ ሊስብ እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ነው።ከሳውዲና ካታር እንዲሁም ከሩስያ ጋር ባለው የጠነከረ ግንኙነቱ ሊወስድ የሚችለው የበቀል ምላሽ ቀላል አይሆንም።የነአብይ አህመድ በኡክሬኑ ጦርነት ላይ ያላቸው ያልጠራ አቋም አገራችንን ለዚያ ሰለባ ያደርጋታል።

በመጨረሻው ላይ ሕዝቡን ጉድ ያስባለው የሳምንቱ  ድርጊት የግንቦት ሰባት ልሳን ሆኖ የኖረው ኢሳት በተባለው የሚዲያ ተቋም ውስጥ የደረሰው የመከፋፈል ቀውስና ንትርክ ነው።ምንም እንኳን ለዚህ ተቋም ጊዜና ትኩረት መስጠቱን ባንፈልገውም ለዓመታት በሕዝቡ ትግል ላይ ያደረሰው ጉዳትና የኤኮኖሚ ዘረፋ ቀላል ስላልሆነ በዝምታ ላለማለፍ ተገደናል።ሌሎቹም የሚዲያ ተቋማት ከተመሳሳይ ውድቀትና ውርደት እንዲድኑ ካለን ፍላጎት በመነሳት መሆኑን እንገልጻለን።በተቋሙ ባልደረቦች መካከል የተነሳው ውዝግብ የኢትዮጵያንና የሕዝቧን ጥያቄ በሚመለከተው ቁም ነገር ሳይሆን በእበላ ባዮቹ  መካከል በተፈጠረ የጥቅም ግጭት ምክንያት መሆኑን እራሳቸው የጋዜጠኛን ሙያ ያረከሱትግለሰቦች ሳያፍሩ ገልጸዋል።እነዚሁ ጉዶች እንደገለጹት የንትርኩ መነሻ ከሕዝብ የተሰበሰበ ከሙቶ ሰማንያ  ሽህ ዶላር በላይ አንደኛው አካል ጠቅልሎ በመውሰዱ ሌላው ስላልደረሰው የተፈጠረ የጥቅም ግጭት ነው። በደመወዝ ቅነሳ ምክንያት የተነሳ ንትርክ መሆኑንም ጨምረውበታል።አዎ ሌባ ሲሰርቅ ይስማማል፣ሲካፈል ይጣላል የሚለው አባባል  ትክክለኛነቱ የታዬበት ድርጊት ነው።ብር አምጡ ነጋ ሌሎቹን በካልቾ መቶ  ለራሱ መጠቅለሉ ካለበት የግለኝነት በሽታ የመነጨ ስለሆነ አያስደንቅም። የተባረሩት “ጋዜጠኞች” እራሳቸውን የገነጠሉና የወጡ በማስመሰል አሁንም የለመዱትን ዘረፋ ለማስቀጠል በሌላ  “ኢሳት ዓለም አቀፍ” በሚል ስም ብቅ ብለናል ብለዋል።አዎ ምን ያድርጉ በዬትኛው ሙያቸው ተቀጥረው ይኑሩ?ዕድሜያቸውን በማውደልደል ከጨረሱ የጡረታ ገቢስ ከዬት ይመጣል?ለወገኖቻችን የምንሰጣቸው ምክር ቢኖር  በመሸም ሰዓት ላይ ቢሆን የሠሩትን ሠርቶ መኖር ይሻላልና እንደሌላውተፋግማችሁ እደሩ የሚል ነው። ሲዘረፍ የሚኖር ጅል ስለማይኖር በከንቱ ባትደክሙ መልካም ነው እንላለን።ሌላው ክንፍ በብርሃኑ ነጋ ጠቅላይነት ከመንግስት ብብት ውስጥ በአዲስ አበባ የመሸገው ሲሆን የሱም ዕድሜ አጭር እንደሚሆን መገመት አያቅትም።አካሄዱን አይተህ ማደሪያውን(መድረሻውን) አስብ ነው።የሙስናውና የጥቅም  ካንሰር በተቋሙ ውስጥ የተሰራጨ ስለሆነ በሁለት ቀርቶ በሶዶ ክትፎ መልክ ቢፈጭ ከሞት አይድንም።ነፍስ ይማር እንላለን።

ለሥርነቀል ለውጥ ሕዝባዊ አመጹን የሚመራ የጋራ አመራር ይፈጠር!!ትግል እስከ ድል!!